# ከመራራ ዛፍ ጣፋጭ ፍሬ አይለቀምም

እንቁስላሴ ወልዱ (wenquselasse@yahoo.com)

ከምርጫና ከሕዝብ ውክልና የተለየ ሕገ ወጥ የሥልጣን መረከቢያ ስልትን ከማራመድ ጋር በተፈጸመ ወንጀል ተከሰው የፍርድ ቤት ቅጣት ተወስኖባቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ከቅጣት ውሣኔው በኋላ ጥፋተኛ መሆናቸውን አምነው፣ በድርጊታቸው መጸጸታቸውን ገልጸው በቀጣይነት ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አክብረውና አስከብረው እንደሚኖሩ በጠየቁት ይቅርታ መሠረት ከእስር መለቀቃቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታም ሆኖ ይታወሳል - የቀድሞው ቅንጅት አመራሮችና አባላቱ፡፡

ይህ ከሆነ ከዓመት በኋላ የቀድሞው ቅንጅት ምክትል ሊቀመንበር የነበሩትና በይቅርታው ከእስር የተለቀቁት ወይዘሪት ብርቱኳን ሚደቅሣ በይፋ ይቅርታ አልጠየኩም በማለታቸው የተሰጣቸው ይቅርታ ተነስቶ ቅጣቱ እንዲፀናባቸው ተወስኖ ወደ ማረሚያ ቤት ሊገቡ ችለዋል፡፡

እኚሁ ግለሰብ ያኔ በይቅርታው ባገኙት ነፃነት ከእስር ከወጡ በኋላ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የተሰኘ ፓርቲ አደራጅተው ፓርቲውን በሊቀመንበርነት የመምራት ዕድልም አግኝተው ነበር፡፡

እዚህ ላይ ማንም ኢትዮጵያዊ እንደሚያስታውሰው ቀደም ሲል በ1997ቱ የሶስተኛው ዙር አገራዊ ምርጫ የአራት ፓርቲዎች ጥምረት የነበረው (መኢአድ፣ ኢዴአፓ መድህን ኢዴሊ እና ቀስተ ደመና) የቀድሞው #ቅንጅት፣ ለአንድነትና ለዴሞክራሲ; በፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከገኘው ፓርቲ ቀጥሎ ከፍተኛውን መቀመጫ አሸንፎ ነበር፡፡

የያኔው ቅንጅት የአገሪቱን ርዕሰ መዲና - አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ ለማስተዳደር የሚያስችለውን የሕዝብ የሥልጣን ውክልና ለማግኘትም በቅቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የአገሪቷን የፖለቲካ ምህዳር ስፋት በተጨባጭ ያሳየ፣ ለአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት ፈር የቀደደን ድል መቀበል አልፈቀደም፡፡ ከዚህ ይልቅ ምንም ተጨባጭና አሳማኝ መረጃ ሳያቀርብ #ድምፅ ተጭበርብሯል፣ ምርጫው ይደገም; የሚል አቋም ይዞ የተሰጠውን ሥልጣን እንደማይረከብ በይፋ ገለጸ፡፡

ምርጫው ከመካሄዱ በፊት፣ ቅንጅት ፍፁም ዴሞክራሲያዊ በነበረው የምርጫ ሂደት የምረጡኝ ቅስቀሳ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአቋም ክርክር መድረክን ተጠቅሞ #ምርጫው መጭበርበሩ አይቀሬ ነው; የሚል አቋም ሲገልጽ ቆይቶ ነበር፡፡

በዚህ አካሄድ ውኹንብር ውስጥ የከተታቸውን የአዲስ አበባና ጥቂት የአገሪቱ ትልልቅ ከተሞች ደጋፊዎቹን ;ምርጫው መጭበርበሩ አይቀርም; በሚል ሲገልጽ

የቆየውን መሠረት ቢስ ወሬ እንደ ማስረጃ ተጠቅሞ መንግሥትን በኃይል ለመናድ አነሳሳ፡፡ በማነሳሳት አልተገደበም፣ የአመፅ ቅስቀሳ ሰለባ ለሆኑ ደጋፊዎቹ ክተት አውጆ፣ ለሁከት አነሳሳ፡፡ ሁከቱ መንግሥትንና ሕገ-መንግሥታዊውን ሥርዓት ለመናድ የሚያስችል አቅም ያልነበረው ቢሆንም አዋኪዎቹ በሕግ አስከባሪዎችና ጥቂት ሰላማዊ ዜጎች ላይ የሕይወት ማጥፋትና የአካል ማጉደል ጉዳቶችን ፈጽመዋል፡፡ የግለሰቦች፣ የሕዝብና የመንግሥት ሐብትና ንብረት አውድመዋል፡፡ ለአንድና ለሁለት ቀናት ያህል ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ገድበው መጠነኛ ኪሣራ አድርሰዋል፡፡ የሕግ አስከባሪዎች የሕዝቡን ደህንነትና ሰላም ለማስከበር በወሰዱት እርምጃ፣ በያኔው ቅንጅት ቅስቀሳና ውዥንብር የሁከቱ ፈፃሚ የነበሩ ጥቂት የዋህ ዜጎች፣ የሕይወትና የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

ይህ ሁከት የተቀሰቀሰባቸው ከተሞች ነዋሪ ዜጎች የሁከቱን መካሄድና ያስከተለውን ውድመት ከሦስተኛ ወገን ምስክርነት አልነበረም ያወቅነው፡፡ አይተነዋል፣ ጉዳቱንም ቀምሰነዋል፡፡ ሁከቱን ማን እንደቀሰቀሰውና እንደመራው በበቂ ሁኔታም ተረድተናል፡፡ ለዚህም የያኔው ቅንጅት በተወሰኑ የግል ሚዲያዎች ያስተላለፈውን የሁከት ክተት ጥሪ አንብቦ ለመረዳት ብዙ አያዳግትም፡፡ በተለይ በተወሰኑ የአዲስ አበባ አካባቢዎች ቅንጅት በጠራውና የአመፅ ውሣኔ ለማስፈፀም #ለአመጽ ተነስ የሚል ጥሪ እስክናስተላልፍ በንቃት ጠብቁ; የሚል መልዕክት የተላለፈባቸው ስብሰባዎች ላይ ተሳታፊ በመሆን፣ (ለመታዘብም ጭምር) እውነታውን ለመገንዘብ አያስቸግርም፡፡

መንግሥትንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ የአመፅ ቅስቀሳ ማካሄድ፣ አመፁን መምራት፣ በአመፅ ላይ መሳተፍ፣ በሰው ሕይወትና አካል፣ በግለሰብ፣ በሕዝብና በመንግሥት ሐብትና ንብረት ላይ ውድመት ማድረስ፣ ሰላማዊ የሕዝብ እንቅስቃሴን መገደብና ሌላም በአገሪቱ ሕገ-መንግሥትና ከዚሁ በመነጨው የወንጀል ሕግ የከተከለከለና የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊት ስለመሆኑ ለማንም በሚገባ አኳኋን በግልጽ ተቀምጧል፡፡

መንግሥት ደግሞ እነዚህን ወንጀሎች በመፈጸም የተጠረጠሩ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ የፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ጥፋተኝነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ እንዲቀጡ በማድረግ ሕግን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ኃላፊነትና ግዴታ ሥልጣን በውክልና በሰጡት ዜጎች የተጣለበት ነው፡፡ ይህን ኃላፊነትና ግዴታውን የመወጣትና ያለመወጣት ጉዳይ ለምርጫ የሚቀርብና በድርድር የሚለወጥ አይደለም፡፡

በዚሁ መሠረት ሰኔ 1997 እና ጥቅምት 1998 ለተፈጸሙት የወንጀል ድርጊቶች ምክንያት የሆነውን ሁከት በማቀናበር፣ በመቀስቀስ፣ በመምራትና በመፈጸም ወንጀል በተጠረጠሩ የቀድሞው ቅንጅት አመራሮችና አባላት ላይ የፌዴራል አቃቤ ሕግ፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ መሠረተ፡፡ በዚህ ወንጀል አቀናባሪነትና መሪነት ተጠርጥረው ክስ ከተመሰረተባቸው ሰዎች ውስጥ አሁን በእስር ላይ የሚገኙት የቀድሞው ቅንጅት ምክትል ሊቀመንበር ወይዘሪት ብርቱኳን ሚደቅሳን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ አመራሮቹና አባላቱ ይገኙበታል፡፡

የፍርዱ ሂደቱ የተከሳሾቹ ቤተሰቦች፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጠኞች ሌሎች ታዛቢዎች በተገኙበት በሦስት ቋንቋዎች (በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛና ፈረንሣይኛ) እየተላለፈ በግልጽ ችሎት ነበር የተካሄደው፡፡ በዚህ የፍርድ ሒደት ተከሳሾቹ አቃቤ ሕግ ያቀረበውን ማስረጃ ተከላክለው ጥፋተኛ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ባለመቻላቸው ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ብይን አሳልፎባቸው እንደየጥፋታቸው ክብደት ከሶስት ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ የእስራት ቅጣት ወሰነባቸው፡፡ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማሰማት መብታቸውን መጠቀም እንደሚችሉም ገልፆላቸው ነበር፡፡፡

ጥፋተኛነታቸው ተረጋግጦ በፌዴራል ከፍትኛ ፍርድ ቤት ቅጣት የተወሰነባቸው እነዚህ ተከሳሾች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አላቀረቡም፡፡ ከዚህ ይልቅ #ጥፋተኝነታቸውን ማመናቸውን፣ በድርጊታቸው መጸጸታቸውን፣ ለወደፊት ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊውን ሥርዓት አክብረውና አስከብረው ለመኖር መወሰናቸውን ገልጸው ይቅርታ እንዲደረግላቸው እያንዳንዳቸው ፊርማቸውን ባኖሩበት ደብዳቤ ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ላኩ፡፡ በአገሪቱ የይቅርታ ሕግ መሠረት በወንጀል ተከሰው የቅጣት ውሣኔ ለተላለፈባቸው ታራሚዎች ይቅርታ ማድረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን ሳይሆን ለዚሁ ጉዳይ በተቋቋመው የይቅርታ ቦርድ ተመርምሮ ቦርዱ ታራሚዎቹ ይቅርታ ማግኘት ይችላሉ ብሎ ሲያምን ለአገሪቱ ፕሬዚዳንት አቅርቦ የሚያስወስን ይሆናል፡፡

ታራሚዎቹ የቀድሞው ቅንጅት አመራሮችና አባላት ይቅርታ የጠየቁበት ደብዳቤ የደረሰው የይቅርታ ቦርድ ማረሚያ ቤት ድረስ በመሄድ ይቅርታ ጠያቂዎቹ ይቅርታ መጠየቃቸውና ፊርማቸው የእነርሱ መሆኑን አንድ በአንድ ጠይቆ አረጋገጠ፡፡ ከዚህ በኋላ ቦርዱ ጉዳዩ ላይ መክሮ #ይቅርታ ሊያገኙ ይችላሉ; ብሎ ስላመነ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ላላቸው የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት አቀረበ፡፡ ፕሬዚዳንቱም የይቅርታ ጥያቄውን አጽድቀው ለእያንዳንዱ ይቅርታ ጠያቂ ታራሚ ዳግም ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት ፈጽመው ቢገኙ ቅጣቱ ይጸናል; የሚል ቅድመ ሁኔታ የሰፈረበት ደብዳቤ እንዲደርሳቸው አድርጎ ያለምንም የመብት ገደብ ይቅርታ ተደርጎላቸው ከማረሚያ ቤት በነፃ ተለቀቁ፡፡ ይቅርታው የተሰጣቸው በውጭ ኃይሎች፣ በደጋፊዎቻቸው ጫና አይደለም፡፡ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት እንጂ፡፡ የቅጣት ውሣኔውም የተላለፈባቸው ይቅርታውንም ያገኙት በሕግ ነው፡፡

ከእስር ቅጣት በነፃ የተለቀቁት የቀድሞው ቅንጅት አመራሮችና አባላት ይቅርታው ባስገኘላቸው መብትና ነፃነት የተወሰኑት የቀድሞ ፓርቲያቸውን ዳግም አደራጅተው የተቀሩትም አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ መስርተው ወደ ፖለቲካ ሕይወታቸው ተመለሱ፡፡ የቀድሞው ቅንጅት ምክትል ሊቀመንበር ብርቱኳን ሚደቅሣ አገር ውስጥ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማካሄድ አዲስ ፓርቲ ካደራጁት አንዷ ነበሩ፡፡ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የተሰኘ ፓርቲ መስርተው የፓርቲው ዋና ሊቀመንበር ሆነው ለመሾምም በቅተው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ወይዘሪት ብርቱካን በጠየቁት ይቅርታ መሠረት ይቅርታ መጠየቃቸው ተረጋግጦ ሰኔ 1999 ዓም ከእስር ተለቀው ወደፖለቲካ ሕይወታቸው ከተመለሱ ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ በቅድመ ሁኔታ የተሰጣቸውን ይቅርታ የሚያስገፍፍ

ድርጊት ፈፅመው ተገኙ፡፡ ስዊድን ለሚኖሩ የፓርቲያቸው ደጋፊዎች በተጠራ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ከእስር የወጡት ይቅርታ ጠይቀው እንዳልሆነ በይፋ ገለጹ፡፡ ይህንንም የውጭ ሚዲያዎች አሰራጩት፡፡

እዚህ ላይ ነው ወይዘሪት ብርቱኳን አጣብቂኝ ውስጥ የገቡት፡፡ ከእስር የወጡት ይቅርታ ጠይቀው ካልሆነ ይቅርታ ሰጪው አካል ይቅርታውን የሰጠው ሳይጠየቅ ወይም በተጭበረበረ ጥያቄ ነው ማለት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ወደ አገር ቤት ሲመለሱ የይቅርታው ሕግ በሚያዘው መሠረት በ20 ቀናት ውስጥ በጠየቁት ይቅርታ መሠረት ከእስር መለቀቃቸውን በይፋ ተናግረው በስዊድን ሥቶክሆልም #ይቅርታ ጠይቄ አይደለም ከእስር የተፈታሁት; በማለት በይፋ የገለጹትን አቋማቸውን እንዲያስተባብሉ ተጠየቁ፡፡ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ብርቱኳን ሚደቅሳ ይህን ከማድረግ ይልቅ #ይቅርታ አልጠየኩም; በሚለው አቋማቸው ጸኑ፡፡ እንዲያስተባብሉ የተሰጣቸው ቀነ ገደብ ሲያበቃ ባልጠየቁት፣ ባላቀረቡት ወይም በተጭበረበረ የይቅርታ ጥያቄ ከእስር መውጣታቸውን ስለሚያመለክት ይህም ሕገወጥ ድርጊት በመሆኑ ተወስኖባቸው የነበረባቸው የዕድሜ ልክ እስራት ቅጣት እንዲጸና፤ የይቅርታ ቦርዱ ወሰኖ ለፕሬዚዳንቱ ባቀረበው መሠረት ይቅርታው ተነሳ፡፡ ይቅርታው የተሰጠው በሕግ እንደነበረ ሁሉ፤ ይቅርታውም የተነሳው ሕግ በሚያዘው መሠረት ሆነ፡፡

ይህን ተከትሎ ከወይዘሪት ብርቱኳን ጋር በተመሳሳይ ክስ የቅጣት ውሳኔ ተላልፎባቸው በይቅርታ ከእስር የወጡት ባልደረቦቻቸው እነርሱም ይቅርታ ጠይቀው መሆኑን ሳይክዱ እንደማንኛውም ዜጋ ባላቸው መብት እየተንቀሳቀሱ የወይዘሪት ብርቱኳን ይቅርታ ተነስቶ ዳግም ማረሚያ ቤት መመለስ የሚቃወም አቋማቸውን ማሰማት ጀመሩ፡፡ በውጭ አገር ያሉ ደጋፊዎቻቸው፣ በመሠረተ ቢስ ውንጀላ መንግሥትን እጅ እንዲሰጥ ማድረግ የሚቻል የሚመስላቸው #ሰብዓዊ መብት አስከባሪ ነን; ባይ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሰላማዊ ሰልፍ በማካሄድና ሀሰተኛ የወሬ ሪፖርት በማሠራጨት ጉዳዩን ማራገቡን ተያያዙት፤ አሁንም አላረፉም፡፡

ወይዘሪት ብርቱኳን የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ የተሰጣቸው ይቅርታ፣ ቅጣቱ ዳግም ፀንቶ ወደእስር የመመለሳቸው ጉዳይ የህግ የበላይነት ጥያቄ እንጂ ለድርድር የሚቀርብ፣ በተወሰኑ ቡድኖች ፍላጎት ሊቀየር የሚችል አይደለም፡፡ ሕግ ሰዎችን በታዋቂነት፣ በሐብት፣ በፖለቲካ አቋም፣ በፆታ እየለየ አንዱ ላይ የሚሰራ ሌላው ላይ ደግሞ የማይሰራ አይደለም፡፡ ሁሉም ሰው ካለምንም ልዩነት በሕግ ፊት እኩል ነው፡፡ የሕግ የበላይነት መርሕም ይሄው ነው፡፡

በመሆኑም ከሕግ አኳያ አንድም ተጨባጭ ማስረጃ ወይም የሕግ መርህ ሳይጠቅሱ መንግሥት ላይ ጫና ለማሳደር #ወይዘሪት ብርቱኳን ትፈታ; የሚል አቋም የያዙና የሚጠይቁ፣ የሚፍጨረጨሩ ወገኖች አካሄድ መሠረታዊውን የሕግ የበላይነት መርሕ የሚፃረር ነው፡፡

የሕግ የበላይነት የሰላማዊ ዜጎች በሕይወት የመኖር ተፈጥሯዊ ሰብዓዊ መብትና ሌሎች ከዚህ የመነጩ መብቶች መከበር ብቸኛ ማረጋገጫ ነው፡፡ መንግሥት ይህን

የሕግ የበላይነት የሚቀለብስ አንድም እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ ብቸኛው የሥልጣን ባለቤትና ምንጭ ሕዝብ መሆኑን፣ ሥልጣን የተረከበውም በሕዝብ ውክልና መሆኑን የተረዳና ይህን የሚያከብር መንግሥት የሕግ የበላይነትን አይጥስም፡፡ ይህን ካደረገ በውክልና የተሰጠውን ሥልጣን ተላልፏል፡፡ አምባገነንነትም ይኸው ነው፡፡ መንግሥት ይህን ፈጽሞ ሲገኝ ሕዝብ በውክልና የሰጠውን ሥልጣን የመቀማት መብት አለው፡፡

ሕግንና የባለሥልጣናትን የሥልጣን ገደብ እያወቁ ሕዝብ ውስጥ ውዥንብር በመንዛት ጭፍን የጥላቻ ስሜት ለመፍጠር የታራሚዋ ወይዘሪት ብርቱኳን እናትና ሕፃን ልጅ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የትፈታልኝ ምልጃ እንዲያቀርቡ የሚያነሳሱና የሚፈጽሙ ይህንኑ የሚያራግቡ ወገኖችም አሉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የታራሚዋ የቅጣት ውሣኔ በጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በሌላ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ በግልም ሆነ በጋራ የመቀየር ሥልጣን የሌላቸው የሕግ የበላይነት ጥያቄ ነው፡፡ የትፈታውን ጥያቄ በቤተሰቦቿ በኩል ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚላክ ማመልከቻ የሚያቀርቡና የሚያራግቡ ወገኖች ዋነኛ ዓላማቸው ጉዳዩ በምርጫ ቢሸነፉ የሕግ የበላይነትን የሚፃረር ሥልጣን ለመመንተፍ በሚያስችል ሁኔታ የሕዝብን ስሜት ይኮረኩራል ብለው ስላሰቡ እንጂ ከዚህ ብቸኛ ሰላማዊና ሕጋዊ የሥልጣን መረከቢያ አካሄድ ውጭ ለሆነ ሕገወጥ አካሄድ ሊሰለፍ የሚችል ዜጋ ዛሬ ሊኖር እንደማይችል ቢያውቁት ይመረጣል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በመጠኑ ከተገለጸው የሕግ የበላይነት መርህ አኳያ የታራሚዋ የወይዘሪት ብርቱኳንን መፈታት መጪው ምርጫ ላይ ለመሳተፍ እንደቅድመ ሁኔታ የማስቀመጥ አዝማሚያ የሚታይባቸው ምናልባት ሕልማቸው ቢሳካ እንኳን የአገሪቱን ሰላም ከማደፍረስ እንደ ከዚህ ቀደሙ የሰላማዊ ዜጎችን ሕይወት ለአደጋ ከማጋለጥ፣ ንብረት ከማውደም ያለፈ አንዳችም በጎ ነገር እንደማያመጡ ሕዝቡ ጠንቅቆ አውቆታልና ቢባንኑ ይበጃቸዋል፡፡ ከመራራ ዛፍ ጣፋጭ ፍሬ እንደማይለቀቅም ቀድሞ ነቅቷልና፡፡